# ሕፅናዊነት - አጭር የግል ማስታወሻ

እሱባለው አበራ ንጉሴ

“ሕፅናዊነት” አዳም ረታ የፈጠረው አዲስ የአጻጻፍ ስልት (Method) ነው። ከአዳም በኋላ የሚነሡ ጸሐፍያን አዋጭ ሆኖ እስካገኙት ድረስ የአኪያየን ስልቱን በድርሰት ሥራቸው ቢከስቱት የሚያስኮንን፣ የሥራቸውንም ዋጋ (credit) የሚያሳጣ አይደለም። እንዲያውም ሕፅናዊነትን እንደ አንድ የትረካ አማራጭ መንገድ በመገልገላቸው ሊበረታቱ ይገባል።

“ሕፅናዊነት” በራሱ ተረክ (story) ሳይሆን የድርሰት አጻጻፍ መሣሪያ (literary device or instrument) ነው።

አዳም ረታ “ሕፅናዊነትን” ለመዘየድ ረዥም ርቀት ለመጓዝ የተገደደው ያለንበትን የዘመን ጠባይ፣ መረባዊ ግንኙነታችንን፣ ውስብስብ ሕይወታችንን፣ ለውጦችን ሳያጓድል ለመግለጽና ለመወከል የሚያስችል ሁነኛ ቴክኒክ ስላጣ ነው።

ወደ “ሕፅናዊነት” ያመጡት ገፊ ምክንያቶች አሉ። ምናልባትም አዳም ረታ ከአንጋፋዎቹ የሀገሩ ከያኒያን ዘንድ ነባራዊውን ዘመንና ግንኙነታችንን በመግለጽ ረገድ የሰመረ የአጻጻፍ ስልት ንድፍ ለማግኘት ቢታደል ኖሮ ድካሙና ኀሰሳው ይቀልለት ነበር። የእነርሱ ፈለግ ላይ የራሱን እሴት ጨምሮ ከመከተል ወደ ኋላ የሚል አይመስለኝም። እኛ ሀገር ሲሆን እንደ እንግዳ ነገር ከተቆጠረ አላውቅም። የሥነ ጽሑፍ ባሕላቸው በዳበረ ሀገራት ውስጥ ይህ የተለመደ ነው።

“ሕፅናዊነት”ን የሚገለገሉ ወጣት ከያኒያንን በግልብ ኂስ ማግለል፣ “ሕፅናዊነት” አዳም ረታ እንደማንኛውም ሰው ኖሮ ሲያልፍ አብሮት ሊሞትና ሊዘነጋ የሚችል የአጻጻፍ ስልት እንደሆነ ያለመገንዘብ ውጤት እንዳመጣው አስባለሁ። ሌሎች ጸሐፊያን ስልቱን አጎልብተው ባይገለገሉበት “ሕፅናዊት” በአዳም ረታ ሥራዎች ብቻ ተወስኖ ይቀራል። ያ ማለት የአጻጻፍ ስልቱ በሌሎች ደራሲያን የሚዳብርበትን፣ የሚያድግበትን ዕድል አያገኝም ማለት ነው።

ደራሲ ሙሉጌታ አለባቸውም በ“መሐረቤን ያያችሁ” መጽሐፉ መግቢያ ከአዳም ረታ የሕፅናዊነትን የአጻጻፍ ስልት የተዋሰበትን ምክንያት ሲያስረዳ “ታሪኮቹ የተዋቀሩበት ዘዴ የአቶ አዳም ረታ “ሕፅናዊነት” የተሰኘ የአጻጻፍ ስልት ነው። እነዚህን ታሪኮችን ለመንገር ተመራጩ ዘዴ ሆኖ ስላገኘሁት አመስግኜ ወስጄዋለሁ። ሕፅናዊነትን የማስቀጠል ደፋር ሙከራዬም ነው!” ሲል የገለጸውም፣ ይህንኑ በመረዳቱ ነው።

አዳም ረታም በ“አብርሆት” መጽሔት ቃለ ምልልሱ ላይ ኮስታራ ከሆነ ወይም የተባ የሥነ ጽሑፍ፣ የባሕል ኂስ ካለበት ኅብረተሰብ እና ልብ ወለዱ እንኳን ንዑስ ዘውጎች ካልተሰየሙለት ዘመናዊ ከተባለ የሥነ ጽሑፍ ባሕል ስለመመዘዙ ያወሳል። ይሄ እጥረት በሆነ መልክ ድጋፍ ያጣ ደራሲ እንደሚያደርገው፣ የራሱን ፍልስፍና ሲናገር በአገራችን የመጻፍ ካርታ ላይ ከማንና የት ጋር እንደምናስቀምጠው ግራ ሊያጋባን እንደሚችልም አልሸሸገም። ይሄ ባይተዋርነት ሆነ ተብሎ ከሚሰነዘር አግላይነት ጋር ሲደመር ሕፅናዊነት የሚለው ቃል ገቺ ወይም አጋጅነት እንደሚኖረውም ገልጿል።

“ሕፅናዊነት”ን ያገኘው በብዙ ኀሰሳና ምርምር ውስጥ አልፎ ነው። በ“ሕፅናዊነት” (በእንጀራና ኢንጀሪ፣ በሥግር ልብ ወለድ) የአጻጻፍ ስልት ላይ የዲበ-አካላዊና አእምሮአዊ ኑባሬ (Metaphysiclal and

Ontological) ጥናቶችን በማድረግ መግለጫ (ማኒፌስት) ያቀረበውም አጽንዖት እንዲሰጥለት ስለፈለገ ነው። ከእርሱ በኋላ የሚመጡ ጸሐፊያን፣ እንደ እርሱ እንዳይዳክሩ “ሕፅናዊነት”ን አዋጭ ሆኖ እስካገኙት ድረስ አጎልብተው እንዲጠቀሙት መነሻ ዳና እና ተሻጋሪ አበርክቶ ለመተው መሞከሩም ነበር።

“ሕፅናዊነት”ን እንደ አንድ የአጻጻፍ ስልት ከመገልገል ባለፈ በተጽዕኖ ያመለጡ ተወራራሽ ጽሑፎች (texts)፣ የገጸ ባሕርያት ምስስሎሾችና ቅጂዎች (imitations) ከአዳም ረታ በሥራዎቹ የተገኙበት ሌላ ከያኒ ሲኖር በአደባባይ መጽሐፍ ገልጦ፣ ገጽ ጠቅሶ መሞገት፣ በተጨባጭ መረጃ አስደግፎ መተቸት ይገባል። እንዲህ  ዓይነቱ ልማድ ደራሲውም ለተጠየቅ ራሱን እንዲያሰናዳ ያደርገዋል። ይህ ካልሆነ ግን በደፈናው የሚነሡ ግልብ አስተያየቶች እርባና አይኖራቸውም። ዘላቂ እሴትንም አይጨምሩም።

ከዚህ ውጪ “በጎ ተጽዕኖ” እንዳለም ልብ ማለት ያስፈልጋል። ልክ ሁሉም የዓለማችን ደራሲ ፍጹም ራሱን በራሱ እንደፈጠረ አድርጎ የመውሰድ ዝንባሌ ስሕተት ነው። ከተጽዕኖ የሚያመልጥ ከያኒ አለ ለማለት ይቸግራል። እንዲያውም በዓለም የተደነቁ ጸሐፊያን አንዳቸው ከአንዳቸው የተዋረሱት የተለያየ “ተጽዕኖ” አለ። ማን ማን ላይ በምን መልኩ ተጽዕኖ እንዳሳደረ የሚያሳዩ ካርታዎችም በጥናት ተደግፈው ይቀርባሉ። ራሳቸው ከያኒያኑም ያለመሸፋፈን ማን ተጽዕኖ እንዳሳደረባቸው ይናገራሉ። እናም “ተጽዕኖን” በደፈናው የማነወር አካሄድም አላዋቂነት አለው።